# <u>የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ</u>

# <u>መተዳደሪያ ደንብ (Bylaws)</u>

# <u>2016 ዓ.ም (እ.አ.አ 2024)</u>



# የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ

## አወቃቀር (structure) 2016(2024)

| ጠቅላላ ጉባኤ | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቦርድ | | | | የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ | | | | |
| ዳይሬክተር (ም/ዳይሬክተር) | | | | | | | | |
| ዋና ጸሃፊ | የህዝብ ግንኙነት ኮሚቲ | የሂሳብና ፋይናንስ ኮሚቲ | የእቅድና ፕርጀክት ጥናት ኮሚቴ | የህግና ማህበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ | የጤናና ስፖርት ኮሚቴ | የትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ | የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ኮሚቴ | የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ |

# አንቅፅ- 1 መግቢያ /መቅድም

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ እ.አ.አ. በ **1983** ዓ/ም የተቋቋመ ማህበር ነው። በጆርጂያ ህግ ኮድ Title **14**-chapter **3** Non-profit Corporation መሰረት በ **501(C) (3) IRC** ስር የሚመራ የመረዳጃ (Charity) ድርጅት ሲሆን በአትላንታና አካባቢው ለሚኖሩ እትዮጵያዊያንና ኢትዮ-አሜሪካዊያን በራሳቸው ፈቃድ በአንድ ጥላ ስር በመሰባሰብና በመደራጀት የሚያጋጥሙንን የህይወት ተግዳሮቶች በጋራ ለመቋቋምና ጠቃሚ የሆኑ ባህላችንን፤ ታሪካችንንና እሴቶቻችንን አዳብሮ ለመጠበቅና ለትውልድ በማስተላለፍ በኑሮ ደረጃችው የተሻሻለ ማህበረሰብ እንዲኖር በትጋት መሥራትና እንዲሁም ከምንኖርበት ሀገር ህግ ጋር በማጣጣም ከማንኛውም፣የዘር፣ የፖለቲካና ሃይማኖት ተጽእኖ ነጻ የሆነ ጠንካራ ማህበር ነው።

# ምዕራፍ አንድ አመሰራረት (ESTABLISHMENT)

# አንቅፅ- 2 ስያሜ:-

**የማህበሩ መጠርያ**: የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ፤

**ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION IN ATLANTA INC (ECAA)** ተብሎ ይጠራል።

# አንቀፅ ፣ 3 የደንቡ ተፈፃሚነት:-

ይህ ደንብ በአትላንታ አካባቢና በመላዉ ጆርጂያ ግዛት ውስጥ በሚኖሩ የማህበሩ አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# አንቀጽ- 4 አድራሻ:-

**5616 MEMORIAL DRIVE, STONE MOUNTAIN, GA 30083** የማህበሩ ፅ/ቤት በአትላንታና አካባቢ የሚኖር ሲሆን ሌሎች ተጨማሪ ፅህፈት ቤቶችን ለመክፈት በምልአተ ጉባኤ ድምፅ የሚፀድቅና በዋናው ፅህፈት ቤት ባጀትና አስተዳደር ብቻ የሚተዳደር ክፍል ነው ።

# አንቀጽ- 5 ትርጓሜ:-

**በዚህ መተዳደርያ ደንብ ውስጥ**:-

**5.1 ኢትዮ አሜርካዊ ማለት**:- በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በዜግነት አሜርካዊ የሆነ ወይም የሆነች ማለት ነው።

**5.2 አትላንታና አካባቢው ማለት**:- ከተማ ውስጥ ወይም በሌሎች የጆርጂያ ግዛት ውስጥ የሚኖር የማህበሩ አባል ማለት ነው።

**5.3 አባል ማለት**:- የአባልነት መመዘኛውን በሚሟላት መብትና ግዴታውን በአግባቡ የሚወጣ ማለት ነው።

**5.4 ቤተሰብ ማለት**:- የትዳር አጋር፣ ልጆች ወይም ወላጆች አንድ ላይ የሚኖሩ ማለት ሲሆን በምኖርበት ጆርጂያ ግዛት ህግ የሚታይ ይሆናል ።

**5.5 ኢ /ኮ/ ማ /አ ( ECAA ) ማለት**:- የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ ማለት ነው።

**5.6 ጠቅላላ ጉባኤ ማለት** :- የማህበሩ የበላይ አካል ሲሆን ሀላፊነታቸውንና ግዴታቸውን የፈፀሙ የማህበሩ ጠቅላላ አባላት ማለት ነው። ጠቅላላ ጉባኤ የሚመራበትን ህገ ደንብ የሚያሻሽልና የሚያፀድቅ በማንኛውም ንብረቱ ላይ የሚወስን የማህበሩ የመጨረሻው ወሳኝ አካል ማለት ነው። **Georgia Code 14-3-1021**.

**5.7 ቦርድ ማለት፡-** በጆርጂያ ህግ **14-3-802-804** ከቀረጥ ነጻ የሆኑ ከተለያዪ በ **501(C)(3)** ስር የተደራጁ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አባል ከሆኑ ብቻ የተመረጡ ተወካዮች እና ከጠቅላላው ጉባኤው በቀጥታ ድምፅ ምርጫ ከተመረጡ የቦርድ አባላት የተዋቀረ ነዉ።

**5.8 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ማለት፡-** በጠቅላላ ጉባኤው በግልፅ አብላጫ ድምፅ የሚመረጡና ማህበሩን የእለት ተእለት ስራ የሚያከናውን ነው።

**5.9 ዳይሬክተር፡-** በጠቅላላ ጉባኤ በቀጥታ አብላጫ ድምፅ የሚመረጡና የስራ አስፈፃሚውን ኮሚቴ በሃላፊነት የሚመሩና ማህበሩን የሚወክሉ ናቸው። **Georgia Code 14-3-841.**

# ምእራፍ ሁለት፡-

# አንቀፅ- 6. አላማ፡- (Objective)

**ማህበሩ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-**

**1.** በአትላንታና አካባቢው በጆርጂያ ግዛት ውስጥ የሚኖሩትን ኢትዮጵያዊያንና ኢትዮ አማሪካዊያን በማቀራረብ የጋራ ባህላቸውንና ታሪካቸውን ቋንቋችውን ጠብቀው ኢትዮጵያዊ አንድነትን የሚያጎለብቱና ታሪክን ለትውልድ የሚያስተላልፍ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

**2.** የሃይማኖት ፣ የጎሳ፣ የጾታ፣ የፖለቲካ ልዩነት ሳይደርግ ማንኛውንም አካል እንደ ማህበረሰብ በጋራ በኢትዮጵያዊነት ጥላ ስር መብቱን ለማስከበር ይችል ዘንድ አንድ ሀገራዊ አንድነት ሀይል መገንባት ነው።

**3.** በሞት፣በህመም ፣ በአደጋ፣ በአካል ጉዳት ወይም በስራ ማጣት የኢኮኖሚ ችግር ሲያጋጥማቸው የማህበሩ አመታዊ በጀት አቅም በፈቀደ መጠን ለአባላት ድጋፍና ዕርዳታ ማድረግ ።

**4.** በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በቦርድ ጥላ ስር ሆነው የተለያዩ የእርዳታ ድርጅቶች በመዋቀር ማህብረሰቡን ተደራጅተው እንዲደግፉ ያበረታታል ይፈቅዳል። የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ደንብንና የ **501(C) (3)** IRC ሕግን ተከትለው እንዲሰሩ ዝርዝር ስራዎቻቸው በውስጥ ደንብ ይገለጻል። ምሳሌ- ኪነ-ጥበበት፣ስፖርት፣ሰዕል፣እድር ፤ ወዘተ ፤ **( Georgia Code 14-3-302 Duration and Power of Corporation).**

**5.** ለትምህርት ፣ለስልጠና፣እካልና አእምሮን ማጎልበቻ የስፖርት ማዘውተርያና ለሁሉም አገልግሎት የሚሆን የኮሚኒቲ ማእከል በአባላት ቀጥተኛ ተሳትፎና በአካባቢው በሚኖሩ ማህብረሰብ ድጋፍ መገንባት ነው።

**6.** በአጉል ባህል ከወንጀል ፣ከመጥፎ ሱስ ፣ እንዲርቁ የምክርና የስልጥና መልሶ ማቋቋምያ(rehabilitation) ድጋፍና ዕርዳታ አመታዊ በጀትን ታሳቢ ያደረገና የማህበሩ አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍና ዕርዳታ መስጠት።

**7.** ወደ አትላንታና አካባቢው አዲስ ለሚመጡ የማህረሰባችን አባሎች ከአሜሪካ ባህልና የኑሮ ዘዴ ጋር የሚተዋወቁበትን የምክር አገልግሎትና ድጋፍ መስጥት ።

**8.** በሀገራችን ኢትዮጵያና በየትኛውም አለም ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ላይ የሰብአዊ መብትና የፍትህ መጓደል ሲከሰት ችግሩን በህግ አግባብ ለመቋቋምና ለመከላከል ትብብር ማድረግና ህብረተሰቡ ዕንዲያቀው የጋራ መፍትሄ ያመቻቻቸል ።

**9.**ማህበረሰባችን በሚኖሩበት አካባቢ የፖለቲካ ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህልና የማህበራዊ ተሳትፎ ዕንዲያጠናክሩ ማበረታታት እንዲሁም እንደየ ዝንባልያቸው የሙያና የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚ ዕንዲሆኑ በአባላትና ከአባላት ውጪ ባሉ ሙያተኞች እንዲደገፉ ማገዝና ማመቻቸት።

**10.** ወጣቶች የሙያ ስልጠናና የነፃ ትምህርት ዕድል ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጥቃሚ እንዲሆኑ ህብረተሰቡን እና ሙያው ያላቸውን በማስተባበር እገዛ ማድረግ።

# አንቀጽ- 7 የገቢ ምንጭ:-

**ማህበራዊ አላማውን ለማሳካት የሚጠቀምባቸው የገቢ ምንጭ:-**

1. ከማህበሩ አባላት የሚከፈል የመመዝገብያና አመታዊ የአባልነት ክፍያ ፤

2. የተለያዩ ዝግጅቶችን ከማድረግ ከሚገኝ ገቢ ፤

3. የፕሮጀክት ሀሳቦችን በማመንጨት (በመንደፍ) መንግስታዊና ለጋሽ ለሆኑ ድርጅቶች በማቅረብ ከሚገኝ የገንዘብ ድጎማ ፤

4. ከበጎ አድራጊ ድርጅቶችና ግለሰቦች እንዲሁም ከማህበሩ አባላት የሚገኝ ድጋፍ ፤

5. ከኮሚኒቲው ማእከልና ከተንቀሳቃሽ ንብረት ከሚገኝ የክራይ ገቢ ናቸው።

# አንቀጽ-8 የአባላት የገንዘብ ክፍያ:-

1. የማህበሩን ደንብ ተቀብሎ የኢ ኮ ማ አ አባል ለመሆን ፈቃደኛ የሆነና የአባልነት መመዝገብያ ወርሃዊ ክፍያ በግለሰብ **$10.00** በቤተሰብ **$ 15.00** ይከፍላል ።

2. እያንዳንዱ የተመዘገበ የማህበሩ አባል አመታዊ ክፍያ በግለሰብ **$ 40.00** በቤተሰብ **$ 60.00** ሲሆን ክፍያውን አቅምና ፍላጎት ያለው በአንድ ጊዜ መክፈል ይችላል ይህ ካልሆነ በአመት ሁለት ግዜ እንዲክፍል የተመቻቸና የማህበሩ አመታዊ ክፍያ ቀደሞ የከፈለ አባል በምልአተ ጉባኤ የሚወሰነው የገንዘብ መጠን ቢጨምርም ወይም ቢያንስ ሂሳቡን በማስተካከል ቀጣይ የሚከፍሉት ላይ ማስተካከያ በማድረግ በጉባኤ የተወሰነውን ተግባራዊ ይሆናል ።

3. በዘመናዊ መልክ በድህረ- ገፅ ክፍያ እስኪጀመርና ማሻሻያ እስኪደረግ የመክፈያ ወራቶች እንደሚከተሉት ናቸው።

   የመጀመሪያው ዓመት ክፍያ ጥር (January) - የሁለተኛው ግማሽ ዓመት ክፍያ ሐምሌ (JULY ) ነው ።

4. የአሜሪካን ህግ_ በሚደነግገው በጡረታ የተገለሉ የማህበሩ አባላት የመመዝገብያና አመታዊ ክፍያ፣ ሃምሳ በሙቶ ቅናሽ (**50%** discount) ይደረግላቸዋል ።

# ምእራፍ ሶስት:-

# አንቀጽ 9 አወቃቀር (STRUCTURE) ፤

የማህበሩ አወቃቀር በጆርጂያ ( Domestic Nonprofit Corporation, Title **14,** chapter **3, 501-(C) (3) code )** ህግ መሰረት የሁለቱን የመንግስትና የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ድልድይ በሆነውና ህጋዊ ተጠያቂነትን በመንተራስ ዉላችን ARTICLE OF INCORPORATION በመከተል የተሰራ የማህበሩን ህገ- ደንብ የማሻሻል ስልጣን በሃላፊነት ላይ ያሉትንም ሆነ የማህበሩን አባላት በቀጥታ የምርጫ ድምፅ በሚያሳትፍ የመጨረሻውን የባለቤትነትና ማህበሩ የኔ ነው የሚለዉ አሳታፊነት ከማጎልበት ሚዛናዊ (check and balance system) መሰረትን በጠበቀ መርህ የተዋቀረ ማህበር ነው።

# አንቀጽ 10 ጠቅላላ ጉባኤ:-

**ጠቅላላ ጉባኤ:-** የኢ ኮ ማ አ ፤ ዓላማውን ለማራመድ የአባልነት ግዴታቸውን የሚወጡ አባላትን በሙሉ ያካተተ ስብስብ ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖረዋል:-

**1.** በማንኛውም የማህበሩ ጉዳይና ደንብ ላይ በተመለከተ ወሳኝና የመጨረሻው አካል ነው።

**2.** የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን፣ የቁጥጥር ኮሚቴ አባላትና ሰባት **( 7)** የቦርድ አባላትን ይመርጣል።

**3.** በአመት አንድ ግዜ በመሰብሰብ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚቀርብለትን የስራ አፈፃፀምና የቦርድ ፣ የፋይናንስ ሪፖርቶች አዳምጦ ውሳኔና መመርያ ይሰጣል።

**4.** የቦርድ ሊቀመንበር:- የቦርዱን **2/3** ድምጽ ድጋፍ ካገኘ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት ይችላል ጠቅላላ ጉባኤውን ይመራል።

**5.** አንድ ሶስተኛ**(1/3)** የማህበሩ አባላት ኮሚኒቲው አደጋ ውስጥ ነው ብለው ካሰቡ ፊርማ አሰባስበው ለቦርድ ወይም ለቁጥጥር ኮሚቴ ስብሰባ የጠራልን ሊሉ ይችላሉ

**6.** የተጓደለ የስራ መስኮች ካሉ በቦታው በምርጫ ይተካል።

**7.** አመታዊ በጀት ያፀድቃል፣ መተዳደርያ ደንቡን ያሻሽላል ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ህግና ደንብን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል ። **Georgia Code 14-3-1021**

**8.** ከማህበሩ መካከል ከግማሽ በላይ በስብሰባ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል።

**9.** በተጠራው ጉባኤ ከግማሽ በላይ አባላት ካልተገኙ የማህበሩ አባላት አስር በመቶኛ(10%). ከተገኙ ከተሰብሳቢው **(2/3)** ስብሰባውን እንዲቀጥል ከተስማሙ ጉባኤው ይካሄዳል። ሆኖም ግን ከጠቅላላ አባላት ውስጥ አስር በመቶ**(10%)** ስብሰባ ላይ ካልተገኙ፤ በተለይም ውሳኔ በሚጠይቁ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ፤ ለሁለተኛ ጊዜ ቦርዱ አባላትን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ስብሰባ በመጥራት፤ ቀርበው የነበሩት አጀንዳዎች በተገኘው አባላት ውሳኔ ያገኛሉ።

# አንቀጽ- 11 ቦርድ ማለት:-

ባላቸው ልምድና እውቀት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና እምነት የሚጣልባቸው፣ ለሌሎች አርያ የሚሆኑ፣ በጆርጅያ ህግ በሚፈቅደው ኮድ መሰረት**14-3-802** እና **804** የተዋቀረና በቀጥታ ድምፅ በጠቅላላው ጉባኤ የተመረጡ ሰባት**(7)** የቦርድ አባላትና በውክልና ከመጡ የቦርድ አባላት ጋር በአስመራጭ ኮሚቴ አማካኝነት በአንድ ላይ በመሆን( በመሰብሰብ) ሊቀመንበር ፣ ም/ሊቀመንበር ፣ ፀሃፊ ይመርጣሉ። ሌሎች የቦርድ አባላት በ IRS የተመዘገቡ **501(C) (3) IRC** ስር ካሉ ከግብር ነፃ የሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ቁጥራቸው ከሃምሳ **(50)** በላይ የሆኑ አባላት ያላቸው ማንኛውም ተቋማት አንድነታችንን ፣ባህላችንን ፣ታሪካችንን ጠብቆ ለማቆየት ብቃታቸውና ልምዳቸው ታይቶ እንድ **(1 )** ወኪል መርጠው በመላክ በምርጫው ቀን ከጠቅላላ ጉባኤው ጋር የትውውቅ ስነ-ስርዓት ይፈፅማሉ። ቦርድ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ነው። **Georgia code 14-3-726**

### ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-

**1.** የስራ አስፈፃሚ የሚሰራውን ማንኛውንም ማህብሩን በተመለከተ ደንቡን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል ፣ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በቦርድ የሚወሰኑ ጉዳዮችን ተቀብሎ ተግባራዊ ያደርጋል፣ በስራ አስፈፃሚ ስር ለሚዋቀሩት ጊዜያዊ የስራ ኮሚቴ (Task force) ቁጥጥርና ድጋፍ ያደርጋል የመቋቋምያ ፍቃድ ይሰጣል።

**2.** የማህበሩን ንብረት ገንዘብ በአግባቡ መያዙንና በስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።

**3.** የስራ አስፈፃሚ የሚያደርጋቸውን የውጪ ግንኙነቶች ከማህበሩ አላማ ጋር የማይፃረሩ መሆናቸውን ይቆጣጠራል ፣ ቦርድ አማካሪ (Advisory) ኮሚቴ በስሩ ማቋቋም ይችላል ።

**4.** በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚቀርብለትን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ አመታዊ በጀትና የፕሮጅክት ሐሳቦችን ( Project proposales) መርምሮ ያጸድቃል ።

**5.** በሶስት **(3)** ወር አንዴ በመሰብሰብ የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ከስራ አስፈፃሚው ያዳምጣል እርማትና የማስተካከያ መመርያ ይሰጣል በባጀት ለመሰራታቸውና ወደፊትም ለሚሰሩት ያፀድቃል።

**6.** የተወከሉት የቦርድ አባላት ተሳታፊ መሆናቸውንና ሁሉም ድርጅቶች በአባልነት መመዝገባቸውንና የሚጠበቅባቸውን አመታዊ ክፍያን ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ እንደሆነ ይከታተላል መረጃ በፅሁፍ ይይዛል ።

**7.** የተወከሉበትን ክፍልና ኮሚኒቲውን ድልድይ በመሆን መረጃ የመለዋወጥና አባላትን ወደ ማህበሩ አስተባብሮ የማምጣት ስራ በዋንኛነት የቦርዱ ነው።

**8.** የስራ እስፈፃሚ ኮሚቴ እርዳታ ከጠየቀና በተጨማሪም የቦርድ አባላት አመታዊ ክፍያን እንዲሰበስቡ ከወከላቸው ከአባላት በመሰብሰብ ለዋናው ገንዘብ ቤት ያስረክባሉ።

**9.** የቦርድ አባላት ማህበሩ የሚጠናከርበትን፣ አባላት ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ዘዴ በማጥናትና በመከታተል ለቦርድ ሊቀመንበር ያቀርባሉ።

**10.** ማህበሩ በጉባኤ ተሰብስቦ በቂ በጀት ኖሮት ሲፀድቅና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን የማበረታቻ ክፍያ መጠን አሰጠንቶ ሲቀርብ በቦርድ ይወሰናል፣ የቋሚና ግዜያዊ ሰራተኞችን ቅጥር የክፍያ መጠን በስራ አስፈፃሚ ተጠንቶ ሲቀርብ ቦርድ ይመረምራል ባጀትን ማእከል ባረገ አሰራር ያፀድቃል።

**11.** ከ ኢ/ ኮ/ ማ/ አ መተዳደርያ ደንብን በማይፃረር መንገድ ቦርድ የራሱን የውስጥ መተዳደርያ ደንብ ያዘጋጃል በጉባኤ ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል።

**12.** ተወክለው የተላኩ የቦርድ አባላትን የወከሏቸውን አባላት የስም ዝርዝር ብዛት በቅጽ አስሞልተው ለዋናው ኮሚኒቲ ፅህፈት ቤት በማቅረብ ከመዝገብ ጋር በማመሳከር ቦርድ ያረጋግጣል ለውጥ ሲኖር ይህንንው ህግ በመከተል ይሰራል።

**13.** ከ **$ 3000.00** በላይ የሚጠይቁ ወጪዎችን በአንድ ግዜ ክፍያ ከሆነ ቦርድ በመመርመርና በባጀት መያዛቸውንም በማየት ያፀድቃል።

# አንቀጽ 12 : የቦርድ ሊቀመንበር:-

የቦርድ ሊቀመንበር፣ በጠቅላላ ጉባኤ ከተመረጠና በውክልና ከተላኩ የቦርድ አባላት ጋር በጋራ በመሰብሰብ ይመረጣል። ተጠሪነቱ ለቦርድ ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-**

**1.**የቦርድ ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል ።

**2.** የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባ በ**2/3** ድምፅ የቦርድ ድጋፍ በማግኘት ስብሰባ ይጠራል በሊቀመንበርነትም ይመራል።

**3.** የቦርድ አባላትን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን በደንቡ መሰረት ስራዎች መተግበራቸውን ያረጋግጣል።

**4.** የቦርድ አባላትንና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሃላፊነታቸውን በብቃትና በትጋት እንዲወጡ ያበረታታል ይደግፋል።

**5.** የቦርድ አባላቱን በተለያየ ኮሚቴ ውስጥ ( task force) በማስገባት ስራውን በቅርበት እንዲከታተሉና ተግባራዊ ለመሆኑ ድጋፍ ያደርጋል።

# አንቀጽ- 13 የቦርድ ም/ ሊቀመንበር:-

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-**

**1.** ሊቀመንበሩ በሌለበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል ።

**2.** በሊቀመንበሩ የሚሰጠውን ተግባራት ያከናውናል ።

**3.** ተጠሪነቱ ለቦርዱ ሊቀመንበር ነው ።

## አንቀጽ- 14 የቦርድ ፀሐፊ:-

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-**

**1.** በሊቀመበሩ በሚሰጠው መመርያ መሰረት የቦርድ አባላትን ስብሰባ ይጠራል ሆኖም ግን ጠቅላላ ጉባኤውን ለመጥራት **2/3** የቦርድ ድምፅ በቃለ ጉባኤ በመያዝ ስብሰባ ይጠራል ።

**2.** የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይይዛል ።

**3** በማንኛውም የቦርድ ስብሰባ ወቅት ያለፈውን ቃለ ጉባኤ በማንበብ በነበሩት አባላት ፊርማ ያፀድቃል።

**4.** የቦርድ ፅ/ቤት ተግባራትን ያከናውናል ፣ መዛግብትንና መረጃዎችን ይይዛል ያደራጃል።

**5.** የማህበሩን አባላት ዝርዝር ይይዛል ።

**6** ወጪ ደብዳቤዎችን ያዘጋጃል በሊቀመንበሩ ወይም በምክትል ተፈርሞ ወደሚመለከተው ያስተላልፋል ገቢ ደብዳቤዎችን ይከታተላል ።

**7.** የቦርዱን ፅ/ቤት የሚመለከቱ ስራዎችን ያከናውናል።

**8.**ተጠሪነቱ ለቦርድ ሊቀመንበር ይሆናል።

**9.** የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት ተሰናባቾችንና የቦርድ አባላትን በሃላፊነታቸው ስር የሚገኙ ንብረት ፣ የሰነድና ሌሎችም ቁሳቁሶች ለአዲሶቹ አባላት በማስረከቡ ሂደት የቁጥጥር ኮሚቴ የሚያቀርበውን ቃለጉባኤና የማስረጃ ፊርማዎች ባግባቡ መከናወናቸውን ያረጋግጣል።

## አንቀጽ- 15 የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ:-

የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላው ጉባኤ የሚመረጡ ሶስት**(3)** የሂሳብና የንብረት አስተዳደር ሙያተኞች ያሉት አካል ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-**

**1.** የማህበሩን የገንዘብና የሂሳብ የንብረት አያያዝ ደንብ በማዘጋጀት ከቦርድ ጋር በመመካከር ማንኛውንም የስራ ህጎች በጉባኤ ሲፀድቁ ስራው ተግባራዊ እንዲሆን ያደረጋል።

**2.** በማህበሩ ስር የሚገኙ ማናቸውንም የገንዘብ ዝውውር ወጪና ገቢ ሂሳብ አያያዝ በደንቡ መሰረት መከናወኑን ይቆጣጠራል ፣ የማስተካከያ እርምትም ይሰጣል፣ በየስድስት ወሩ ከቦርድ ጋር በመሆን በማናቸውም ጊዜ የገንዘብ አሰራርን ህጋዊነት የማጎልበትና በራሱም ይሁን ከቦርድ ጋር በመመካከር ግልፅ ያልሆኑ የማህበሩን አሰራሮች ለማረም ለጉባኤው የማቅረብ ሙሉ ህገ- ደንባዊ ስልጣን አለው።

**3.** ማናቸውም በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ስም የሚደረጉ ህትመቶችና፣ ማስታወቅያ ወይም ለሽያጭ የሚቀርቡ ትኬቶች፣ የኮሚኒቲውን አርማ (Logo) መኖር አለበት።

- **(1)**-የደህንነት ማረጋገጫ ምልክቶች(security hologram) እንዲኖር ማደረግ ፤
- **(2)**- የሽያጭ ትኬቶች ስድስት **(6)** አሃዞች(digits) የሚኖሩትና ቅደም ተከተሉን የጠበቁ እንዲሆን ፤
- **(3)**- ትኬቶች ላይ ባር ኮድ ያላቸው መሆኑን ፤
- **(4)**- ለሽያጭ ከመቅረባቸው በፊት የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ብዛታቸውንና ደረጃውን መርምረው የጸደቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

**4.** በአመት አንድ ጊዜ ለቦርድና ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል።

**5.** እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ የገንዘብ ወይም የስራ አፈፃፀም ምርመራና ኦዲት በማድረግ ለቦርድና ለጠቅላላ ጉባኤው ያሳውቃል ፣ በሶስቱም የቁጥጥር ኮሚቴ ከታመነበትና ማህበሩን አደጋ ላይ ይጥላል ብለው ባመኑበት በማንኛውም ጉዳይ ላይ ጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ የመጥራት ስልጣን አለው።

**6.** የማህበሩ መተዳደርያ ደንብ በሁሉም የስራ ክፍሎች በተግባር ላይ መዋሉን እቅዶችና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀትና የጊዜ ገደብ መከናወናቸውን ያረጋግጣል።

**7.** በቦርድና በስራ እስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ጥሪ ከተደረገላቸው በመገኘት ምክርና አስተያየት መስጠት ይችላሉ ፣ በድምፅ አሰጣጥ አይሳተፉም።

**8.** የቦርድና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን ከመጠናቀቁ ከሁለት**(2)** ወር በፊት ዝርዝር የኦዲት ሪፖርት ያዘጋጃል። የርክክብ ሰነድ በማዘጋጀት አዲሱን የኮሚኒት አመራሮች ከነባሮቹ ጋር የሰነድና የሃላፊነት ልውውጥ እንዲፈራረሙ ለአስመራጭ ኮሚቴ ያመቻቻል፣ በሰነድ ርክክቡ ላይ አንዱ ተሸኚና በአዲሶቹ የሚተካ በመሆኑም፣ ለአስመራጭ ኮሚቴው ሙሉ የማረካከብያ ድጋፍ ይሰጣል።

**9.** በቦርድና በስራ አስፈፃሚ መካከል በማንኛውም ጉዳይ ላይ ህገ- ደንቡ ያላያቸው የስራ ክፍተት ቢፈጠር የቦርድ ሃላፊነት እንድተጠበቀ ሆኖ፣ ጉዳዩን የቁጥጥር ኮሚቴ በማየት ስራው እንዲሰራና እስከ ምልአተ ጉባኤው ድረስ የቁጥጥር ኮሚቴው የወሰነው ሀሳብ ገዢ በመሆን ስራዎች ያለማጓተት ተግባራዊ ይሆናሉ።

10. የኦዲትና ቁጥጥር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ነው።

# አንቀጽ- :- 16 - የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ:-

የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤ በግልፅ በአብላጫ ድምፅ አስራ ሁለት(12) አባላት የሚመረጥና የማህበሩን እለታዊ ስራዎችን የሚያከናውን ሲሆን ተጠሪነቱ ለቦርድ ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-**

**1.** የማህበሩን እለታዊ የስራ እንቅስቃሴ ያከናውናል።

**2.** አባላትን በመመዝገብ ዝርዝር መረጃ በዘመናዊ መልክ ይይዛል ።

**3.** ኢ/ ኮ/ ማ/ አ ህጋዊ ወኪል ሲሆን ፣ ማህበሩን በመወከል የውጪ ግንኙነት ተግባራትን ያከናዉናል፣ ይደራደራል።

**4.** ማህበሩን የሚያጠናክሩ አመታዊ ባጀትን ታሳቢ ያደረገ እቅድ በመንደፍ በቦርድ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል።

**5.** ከአመታዊ በጀት ውጪ የሆኑትን ትላልቅ እቅዶችን ቦርድ ካመነበት ለምልአተ ጉቤኤው በማቅረብ ሲፀድቅ በስራ ላይ ያውላል።

**6.** በሶስት**(3)** ወር አንዴ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት በፅሁፍ ያዘጋጃል፣ ለቦርድ ያቀርባል ።

**7.** የማህበሩን አባላት በመተዳደርያው ደንብ መሰረት ተገቢውን አገልግሎት ማግኘታቸውን ያረጋግጣል ፣ ግዴታቸውን እንዲወጡ ክትትል ያደርጋል።

**8.** የማህበሩን አመታዊ ባጀትና የስራ እቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል።

**9.** ለስራ ክንውን የሚሆን የሰራተኛ ቅጥር ያዘጋጃል በቦርድ ሲፀድቅለት ተግባራዊ ይሆናል በተጨማሪም በስራ አስፈፃሚ **2/3** ድምጽ ለሚሰናበቱ ሰራተኞች የቦርድ ውሳኔ የመጨረሻው ይሆናል።

**10.** የማህበሩን አላማ ለመተግበር የገንዘብና የቁሳቁስ ፍላጎት ለማሟላት የተለያዩ የገንዘብና ማቴሪያል ማሰባሰብያ ዘዴዎችን በመንደፍ በቦርድ ሲፀድቅ በተግባር ያውላል።

**11.** እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን በማቋቋም አጣዳፊ ስራዎች እንዲከናወኑ ለቦርድ በማቅረብ ሲፀድቅ ተግባር ላይ ያውላል ።

**12.** የማህበሩን ገንዘብ ፣ ንብረት መረጃዎች በጥንቃቄ መያዛቸውን ያረጋግጣል።

**13.** በወር አንድ**(1)** ጊዜ መደበኛ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ በማድረግ የየኮሚቴዎችን የስራ እንቅስቃሴዎች ይገመግማል ፣ አቅጣጫና መመርያ ይሰጣል።

**14.** ከ **$ 3000.00** በላይ የሚጠይቁ ክፍያዎችን በቦርድ ታይተው እንዲፀድቁ ያደርጋል።

**15.** የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ የሚጠራውና የሚመራው በዳይሬክተሩ ሲሆን ከኮሚቴው አባላት መካከል **1/2** ከተገኙ ስብሰባ ማድረግ ይችላሉ የውሳኔ ሃሳብ ለመስጠት ከአመራሩ **2/3** ኛው የስራ አስፈፃሚ መገኘት አለበት።

# አንቀጽ_ 17 ዳይሬክተር:-

የኢ/ ኮ/ ማ/ አ ዳይሬክተር በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በሃላፊነት የሚመራ ሲሆን ተጠሪነቱ ለቦርድ ነው። የኮሚኒቲው አቅምና በጀት ሲፈቅድ በዳይሬክተሩ ስር የሚመራ ለኮሚኒቲው የተለየ ጥቅምና እድገት የሚያስገኝ ስራ ሲገኝ ተቀጥሮ የሚሰራ ሙያተኛ ይኖረዋል በቦርድ ሲፀድቅ ተግባራዊ ይሆናል።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-**

**1.** የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይመራል ያስተዳድሬል።

**2**. በቦርድ አባላት ስብሰባ ላይ ይሳተፋል፣ ድምፅ መስጠት አይችልም ።

**3.** ማህበሩን በመወከል የውጪ ግንኙነት ያደርጋል **14-3-841 Georgia Code**

**4.** የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በዚህ መተዳደርያ ደንብ የተሰጣቸውን የስራ ሃላፊነት በብቃት መወጣታቸውን ያረጋግጣል ይከታተላል።

**5.** የስራ እቅዶችንና ፕሮጀክት በግዜው መፈፀማቸውን ይቆጣጠራል።

**6.** በኮሚቴ አባላት መካከል መልካም የስራ ምክክርና መግባባት እንዲኖር ያበረታታል።

**7.**የማህበሩን ገንዘብና ንብረት በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል ፣ የተዝረከረከ አሰራርና ብክነትን ሲታይ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ ይወስዳል።

**8.** ለስራ ማስኬጃና ለማህበረሰቡ ተግባር በውጪ ማዘዣ ቅጽና ቼክ ላይ በሂሳብ ሹሙ ከተረጋገጠ ብኋላ ይፈርማል።

**9.** የኮሚኒቲውን አባላት የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ በሚመለከት የውስጥ መመርያ ያዘጋጃል ቦርድ አምኖበት በጉባኤ ከፀደቀ በስራ ላይ ይውላል፣ የውሳኔ አሰጣጡ በተለይም ከስራ ማገድ ከሆነ **3/4** የኮሚቴ አባላት ሲስማሙና በቦርድ ሲፀድቅ ተግባር ላይ ይውላል- አባሉ የተወሰነበት አግባብ ካልሆነ፣ ጉዳዩን ለቁጥጥር ኮሚቴ አሳውቆ በህግ አግባብ ሊጠይቅ ይችላል። በህግ አግባብ ታይቶ የተወሰነው ስህተት ከሆነ ካሳ በመካስና ውሳኔውን የሰጡት አመራሮች ጉባኤው የመቅጣትም ይሁን ከሃላፊነት የማገድ ውሳኔ ሊያሳልፍ ይችላል።

**10.** በቦርድ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

# አንቀጽ 17-1 ረዳት ዳይሬክተር:-

በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱ:-**

**1.** ዳይሬክተሩ በማይገኝበት ጊዜ እንደ ዳይሬክተር ሆኖ ይሠራል ።

**2.-** በዳይሬክተሩ የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

**3.** ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው።

# አንቀጽ 18 ዋና ፀሃፊ :-

ዋና ፀሐፊው በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ጽ/ቤት በበላይነት የሚያስተዳድር ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት:-**

**1.** የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ጽ/ቤት ያስተዳድራል።

**2.** ወጪና ገቢ ደብዳቤዎችን ይቀበላል፣ ለሚመለከታቸውም የስራ ክፍሎች ያሰራጫል በቅደም ተከተል ፋይል ያደርጋል በዘመናዊ አሰራር እንዲቀየር ከሚመለከታቸው ጋራ በመነጋገር ወደ ተግባር ይቀይራል ።

**3.** የማህበሩ አባላትን ዝርዝር መረጃ በሃላፊነት ይይዛል ።

**4.** የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባን በዳይሬክተሩ ሲፈቀድ ይጠራል፣ የስብስብውን ቃለ ጉባኤ ይይዛል ፣ ያለፈውን ቃለ ጉባኤ በማንበብ በነበሩት አባላት ፊርማ ያፀድቃል፣ በቅድመ ተከተልም መረጃውን ፋይል ያደርጋል።

**5.** የማህበሩን ጽ/ቤት ለአባላት ክፍት እንዲሆን እቅድ በማውጣት በኮሚቴው ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

**6.** የጽ/ቤት ቁሳቁሶችን ፍላጎት ዝርዝር በመስራት በጀት ይጠይቃል፣ እለታዊ የስራ ማስኬጃ የገንዘብ ወጪዎች ለዳይሬክተሩ ያመቻቻል በሰነድና የተሟላ ደረሰኝ መኖሩን ያረጋግጣል።

**7.** የየኮሚቴዎቹን የስራ ፕሮጀክት እቅዶች በተወሰነላቸው የግዜ ገደብና በጀት መከናወናቸውን በመከታተል፣ ለዳይሬክተሩ ሪፖርት ያቀርባል።

**8.** በዳይሬክተር የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

# አንቀጽ 19 የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ:-

የህዝብ ግንኙነት ኮሚቴ አስተባባሪ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን፣ ሙያተኛ ቢሆን ይመረጣል፣ የማህበሩን የስራ እንቅስቃሴ በህዝብ መገናኛ ብዙሃን፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በሬዲዮና በኢንተርኔት የሚሰራጩ መረጃዎችን የሚያቀርብ ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ይሆናል። -

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት:-**

**1.** የማህበሩን አላማና የስራ እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ያሰራጫል።

**2.** የማህበሩን ድረገጽ (web- site) ያስተዳድራል ፣ ወቅታዊ መረጃዎችን ያስቀምጣል።

**3.** የጠቅላላ ጉባኤውን የቦርዱና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን ስብሰባ በቪዲዮ በመቅረፅ ፋይል ያደርጋል ።

**4.** የኮሚቴዎቹን ዐብይ የስራ እንቅስቃሴ በቪዲዮ በመቅረፅ ለህዝብ የሚያስተላልፍበትን መንገድ ያዘጋጃል።

**5.** የማህበሩን እንቅስቃሴ ለአባላት ለማሰራጨት በየ ስድስት**(6)** ወሩ መፅሄት ያዘጋጃል ያሰራጫል ።

**6.** ለስራው እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ዝርዝርና በጀት ያቀርባል፣ ሲፈቀድ በስራ ላይ ያውላል።

**7.** በወቅታዊ ጉዳዮች የሚመለከታቸውን ሃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ለአባላት የሚሰራጭ መረጃዎችን አቀነባብሮ ያዘጋጃል ።

**8.** በኮሚቴው ውስጥ በፈቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉትን በመመልመል በኮሚቴው ሲፈቀድ በስራ ላይ ያውላል።

**9.** ማንኛውንም የጽሕፈትና የኤሌክትሮኒክ የቃል መጠይቅ መግለጫዎችን ሁሉ ከመተላለፉ በፊት በዳይሬክተሩ መፈቀዱንና መጽደቁን ያረጋግጣል ።

**10.** በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 20 የሂሳብ ሹም:-

ከአባላት የሚሰበሰውን፣ ለፕሮጀክት ማስፈፀምያ በእርዳታ የሚገኙና በተለያዮ የገቢ ማሰባሰብያ ዘዴዎች የሚገኙ ገንዘቦችን በሃላፊነት የሚያስተዳድር ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል ፣ የሂሳብ ሹም ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው። -

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም:-**

1. የማህበሩን አባላት በግዜው የመመዝገቢያና አመታዊ ክፍያዎችን እንዲፈፀሙ ይከታተላል በዘመናዊ መልክ የመዝገብ አያያዝና ህጋዊ የሂሳብ አሰራርን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ ።
2. ከዳይሬክተሩ ጋር በወጪ ማዘዣ ላይ ይፈርማል፣ የተፈቀደው የገንዘብ ወጪ ከባጀት ጋር መዛመዱን ያመሰክራል።
3. ማንኛውም የገንዘብ ወጪ ከመፈረሙ በፊት የወጪ ማዘዣ ቅጽ በዳይሬክተሩ ወይም በወኪሉ መፈረሙን ያረጋግጣል ። በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም በቦርድ የተወሰኑ እለታዊ ወጪዎችን ተቀብሎ ይፈጽማል።
4. የገቢ ማሰባሰብያ እቅዶችን ከሌሎች የሚመለከታቸው ኮሚቴዎች ጋር ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድ በስራ ላይ ያውላል።
5. የገቢና የወጪ ዝርዝር ሪፖርት በየወሩ መጨረሻ ላይ በማዘጋጀት ለዳይሬክተሩ ያቀርባል።
6. የገንዘብ ገቢና ወጪ ሰነዶች ተገቢውን የሂሳብ አያያዝ ደንብ የተከተሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል።
7. የማህበሩን የሂሳብና የገንዘብ ሰነድ በማንኛውም ጊዜ ለቁጥጥርና ለኦዲት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል።
8. ስራውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ጆርናሎች፣ ሰነዶች ዝርዝር በጀት በማቅረብ ሲፈቀድ በስራ ላይ ያውላል ።
9. ማንኛውም ወደ ማህበሩ የሚላኩ ገንዘቦችን ደረሰኝ በማዘጋጀት ለላኪው እንዲደርሰው ያደርጋል፣ ደረሰኙም የማህበሩ አርማ ያለበትና የቁጥር ቅደም ተከትል የያዘ መሆኑን ያረጋግጣል።
10. በየሶስት(3) ወሩ የሚዘጋጀው የፋይናንስ ሪፖርት በማህበሩ ድህረ- ገጽ ላይ እንዲወጣ ያደርጋል።
11. ማንኛውንም የማህበሩ ክፍያ ወይም እዳዎችን ተከታትሎ በመንግስትም ይሁን በግል ድርጅቶች በወቅቱ መፈፀማቸውንና የፌደራልና የስቴት ታክስ ክፍያዎች ለመፈፀማቸው ሃላፊነት አለበት።

## አንቀጽ 21 ገንዘብ ያዥ:-

ገንዘብ ያዥ ከአባላት የሚሰበሰበውን፣ ለፕሮጀክት ማስፈፀምያ በእርዳታ የሚገኝና በተለያዩ የገቢ ማሰባሰብያ ዘዴዎች የሚሰበሰቡ ገንዘቦችን የባንክ አሰራር ህግን በመከተል በሃላፊነት የሚሰራና የሚጠብቅ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ይመረጣል፣ ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም:-**

1. የማህበሩን ገንዘብ በዘመናዊ አሰራር በመያዝ በባንክ በኩል ያለውን ቀጥተኛ አሰራር የመከታተል ሃላፊነት አለበት ።
2. በማንኛውም መልኩ የተሰበሰቡ ገንዘቦችን በ 24 ሰአት ውስጥ መግባቱን ያረጋግጣል ።
3. ከዳይሬክተሩ ጋር በመሆን በወጪ ቼክ ላይ ይፈርማል፣ በዳይሬክተሩ መፈረሙን ያረጋግጣል ።
4. ማንኛውንም የሂሳብ ሰነዶች በተጠየቀ ጊዜ ለቁጥጥርና ለኦዲት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል ።
5. ገንዘብን በተመለከተ በማንኛውም መልኩ ለኮሚኒቲው የሚገቡም ሆነ የሚወጡ ህጋዊ በሆነው የኮሚኒቲው ደረሰኝ ተረክቦ ለሂሳብ ሹሙ አንድ ኮፒ ያስቀራል። የባንክ ደረሰኞችንም አንድ ኮፒ ለሂሳብ ሹም ይሰጣል።
6. የማህበሩን ቼክ በጥንቃቄ ይይዛል፣ የባንክ ሂሳብ ደብተሮችን በተገቢው ቦታ መሆናቸውን ያረጋግጣል ፣ የሚፈረሙ ፊርማዎች በማንኛውም ኮፒ ላይ በግልፅ እንዲታዩ ጥንቃቄ ይወስዳል ።
7. በዳይሬክተር የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል ።

# አንቀጽ 22 የእቅድና ፕሮጀክት ኮሚቴ:-

የእቅድና ፕሮጀክት ጥናት ኮሚቴ አስተባባሪ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን በስሩ የእቅድና የባጀት የፕሮጀክት ሃሳብ ጥናት ሙያተኞችን በመመልመል፣ የማህበሩን የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ የፕሮጀክት ሃሳቦችን ያዘጋጃል። ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ሲሆን፣

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም:-**

**1.** ከሁሉም ኮሚቴዎች የሚቀርቡ ፍላጎቶችን በማቀናጀት የማህበሩን አመታዊ በጀትና እቅድ ያዘጋጃል።

**2.** የማህበሩን እድገትና ፍላጎት ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ የረጅም ጊዜ የስራ እቅድ ያዘጋጃል።

**3.** የፕሮጀክት ሃሳቦችን ያመነጫል፣ በስራ አስፈፃሚና በቦርድ ሲፈቀድ ዝርዝር ጥናት በማዘጋጀት ለለጋሽ ድርጅቶች (donors) መላኩን ይከታተላል ።

**4.** የተፈቀዱ ፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ይከታተላል ፣ ለለጋሽ ድርጅቶች ያፈፃፀም ሪፖርት በስምምነቱ መሰረት በግዜው መላኩን ይከታተል ።

**5.** ማህበሩን ሊደግፉ የሚችሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ዝርዝር በማጥናት ሲፈቀድ ፕሮጀክቶች ተዘጋጅተው እንዲላኩ ያደርጋል።

**6.** ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል።

# አንቀጽ 23 የህግና ማህበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ :-

የህግና ማህበራዊ ጉዳይ አስተባባሪ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ ሲሆን፣ በስሩ የቤተሰብ ችግር ጉዳይ፣ የኢምግሬሽን ህግ ጉዳይ ሙያተኞችን በፈቃደኝነት በመመልመል ለማህበሩ አባላት ሰፊ አገልግሎት የሚሰጥ ክፍል ሲሆን፣ ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም:-**

**1.** በስራ እጦት፣ በጤና ምክንያት ፣ በዕድሜ ፣ በጾታና በመሳሰሉት ችግሮች ሰለባ የሆኑ የማህበሩ አባላት ተገቢውን ድጋፍ የሙያ ምክርና እርዳታ እንዲያገኙ ያደረጋል።

**2.** ችግር ያጋጠማቸው አባላት ተገቢውን እርዳታና ድጋፍ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

**3.** አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጵያዊያን ከአካባቢው ጋር እንዲተዋወቁ የምክር የሞራልና ካስፈለገም ችግር ላለባቸው የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ እንዲያገኙ በማጥናትና በማቅረብ ሲፈቀድ በስራ ላይ ያውላል።

**4.** አዲስ ለሚመጡ ኢትዮጵያዊያን ስራ የማፈላለግ ምክርና ጥቆማ፣ የስራ ማመልከቻ አሞላልና ምክርና እርዳታ የደርጋል።

**5.** ለራሳቸውም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ለማምጣት ለሚፈልጉ አባላት የኢምግሬሽን ምክርና አገልግሎት ይሰጣል።

**6.** አመታዊ የኢትዮጵያ ቀን ዝግጅት በሃላፊነት ይመራል፣ ዝግጅት ያቅዳል፣ ያስተባብራል።

**7.**ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል።

# አንቀጽ 24 የጤናና ስፖርት ኮሚቴ:-

የጤናና ስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጥ ሲሆን፣ በስሩ ፈቃደኛ የሆኑ ሃኪሞች፣ ነርሶችና የስፖርት ባለሙያዎችን በማሰባሰብ ፣ ለማህበሩ አባላት አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ የሚያመቻች ሲሆን፣ ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው።

**ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነት:-**

**1.** የማህበሩ አባላት ስለ ወቅታዊ የጤና ችግሮች ፣ ትምህርትና መግለጫ በማዘጋጀት በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን ያሰራጫል፣ ያስተምራል ። በአካባቢያችን የሚታዩ ችግሮችን በማጥናት፣ ተገቢውን የመከላከያ የመቆጣጠሪያ መረጃ ለአባላት ያሰራጫል።

**2.** በተለያዩ ምክንያቶች ህክምና ለማግኘት ችግር ያለባቸው አባላት በነፃ እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣አቅም ላላቸው ግሩፕ ኢንሹራንስ በቅናሽ የሚያገኙበትን ሁኔታ በማጥናት መረጃ ይሰጣል።

**3.** የቋንቋ ችግር ያለባቸው አባላት ወደ ህክምና ሲሄዱ አገልግሎት ይሰጣል።

**4.** ወጣቶችና ጎልማሶች ከአጉል ባህል እንዲርቁ በስፖርትና ባህል ጥንካሬ ያሰለጥናል፣ የማህበሩ የስፖርትና ባህል ማእከል እንዲቋቋም ፐሮግራም በመንደፍ ሲፈቀዱ በስራ ላይ ያውላል።

**5.**ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል።

# አንቀጽ 25 የትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ:-

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በዋንኛነት የተቋቋመበትና በ **IRS** ከግብር ንጻ የሆነው ባህሉንና ታሪኩን ለመጠበቅ በመሆኑ የትምህርትና ስልጠና ኮሚቴ አስተባባሪ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን በስራ ፈቃደኛ የሆኑ ይኮምፒዩተር ስልጠና፣ የቋንቋ ማሻሻያ(እንግሊዝኛ) ፣ ለወጣቶች የአማርኛ ቋንቋ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው።

**-ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም:-**

**1.** አዲስ ለሚመጡ አባላት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማሻሻያ ስልጠና ይሰጣል ።

**2.** የኮምፐዩተር ስልጠና ለሚሹ አባሎች ስልጠና ይሰጣል።

**3.** ለወጣቶችና ህፃናት የአማርኛ ማንበብና መፃፍ ስልጠና ይሰጣል ።

**4.** የኢትዮጵያ ልዩ ባህልና ታሪክ ለወጣቶች ትምህርት ይሰጣል ።

**5.**ለስራው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ዝርዝርና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድ በተግባር ያውላል።

**6.** ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል።

# አንቀጽ 26 የሴቶችና የህፃናት ጉዳይ ኮሚቴ:-

የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባሪ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን ሁለት ፈቃደኛ ረዳቶችን በመመልመል ፣ በሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ላይ ያተኮረ ስራዎችን ታከናውናለች፣ ተጠሪነቷ ለዳይሬክተሩ ነው።

**-ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም:-**

**1.** የማህበሩ አባል የሆነች ሴትን በጾታቸው የሚደርሱ ችግሮችን ጥቆማ በመቀበልና በማጥናት ድጋፍና እርዳታ እንዲያገኙ ታደርጋለች ።

**2.** ሴቶች እህቶቻችን እንዲደራጁ ታበረታታለች።

**3.** ሴቶች በሚሰሩበት ቦታ፣ በሚኖሩበት አካባቢ የሚደርስባቸውን በደል በመከታተል፣ የምክር ካስፈለገም የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ ታደርጋለች።

**4.** ሴቶች እህቶቻችን የሀገራቸውን ባህልና ሙያ የሚያንፀባርቁ ተግባራት በጋራ እያዘጋጁ ለአካባቢው ህዝብ እንዲያሳውቁ ታደርጋለች።

**5.** አቅም የሌላቸውና በስራ ላይ የተሰማሩ ወላጆች የህፃናት መዋያ፣ ከትምህርት ቤት መልስ ማቆያና አገልግሎት መስጫ ቦታ በማቀድ ሲፈቀድና በበጀት ሲደገፍ በስራ ላይ ታውላለች።

**6.** ሌሎች በዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ስራዎች ያከናውናል።

## አንቀጽ 27 የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ:-

የወጣቶች ጉዳይ ኮሚቴ አስተባባሪ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን፣ ሁለት ወጣቶችን በመመልመል፣ በወጣቶች ጉዳይ ላይ ያተኮረ ስራዎችን ያከናውናል፣ ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ነው።

**-ዝርዝር ተግባርና ሃላፊነቱም:-**

1. ወጣቶች የማህበሩ አባል እንዲሆኑ ይቀሰቅሳል፣ ያበረታታል።

2. ከሀገራቸው ባህል ጋር እንዲተዋወቁና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል ።

3. ወጣቶች ከጎጂ ባህል እንዲርቁ ቅስቀሳና መረጃ ይሰጣል ።

4. ለወጣቶች መልካም አርአያ የሚሆኑ ጎበዝ ተማሪዎችን፣ ስፖርትኞችን ወዘተ በመጋበዝ ጥሩ ምሳሌ እንዲሆኑ የወጣቶች ስብሰባ በማዘጋጀት በመገናኛ ብዙሃን ያስተዋውቃሉ ።

5. ወጣቶች ባህልቸውን አክባሪ፣ ቤተሰባቸውንና ወገናቸውን አፍቃሪ እንዲሆኑ የማበረታቻ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶችን ያቀነባብራል ።

6. ፈቃደኛ የሆኑ ወጣቶች፣ ለህፃናትና በትምህርት ሂደት ችግር ላለባቸው ወጣቶች በትርፍ ጊዜያቸው ትምህርት እንዲሰጥ ያደርጋል ፣ ያስተባብራል።

# ምእራፍ አራት አባልነት ( Membership)

## አንቀጽ 28 የአባልነት መመዘኛ:-

የማህበሩ አባል ለመሆን የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ይኖርበታል።

1. ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮ አሜሪካዊ የሆነ/ች ።

2. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ተረድቶ የተቀበለና የአባልነት ማመልከቻ ያሟላ/ች።

3. የመመዝገብያ ክፍያውንና አመታዊ ክፍያ ያጠናቀቀ/ች።

4. እድሜ ከአስራ ስምንት (18 ) አመት በላይ የሆነ/ች።

## አንቀጽ 29 የአባላት መብት:-

1. በመተዳደርያ ደንብ መሰረት ሁሉም አባላት በእኩል የማህበሩ አገልግሎቶችን ተጠቃሚ የመሆንና ለማህበሩ አዲስ ተመዝጋቢዎች ከስድስት (6) ወር በኋላ በአመራርነት ተመርጠው የማገልገል መብት አላቸው።

2. በስብሰባ ላይ ያለምንም ገደብ ሀሳባቸውን የመግለፅ መብት አላቸው።

3. አመራሮችን በደንቡ መሰረት ለመምረጥና ለመመረጥ እኩል መብት አላቸው።

4. በህመም፣ በአደጋ፣ በስራ ማጣት፣ ችግሮች ምክንያት የመመዝገቢያና አመታዊ ክፍያ ለመክፈል አቅም ያለመኖር ሲገጥም በነፃ የማህበሩ አባል የመሆን ህጋዊነት መብት አላቸው። ( በጆርጂያ ሕግ የሚታይ ይሆናል )።

5. ማህበሩ በሚመራበት ደንብ ላይ የመወያየትና በጉባኤው የማፅደቅና የመሳተፍ ግለሰባዊ መብቱን ባብልጫ ድምፅ ተገዢ የመሆን ሙሉ መብት አለው።

6. በማህበሩ ጉዳይ ህግ ለማስከበር አንድ አባል ይግባኝ በማለት የመክሰስና የመከሰስ መብት አለው።

7. ግለሰባዊ መብቱም ይሁን ማህበሩ አደጋ ላይ መሆኑን ካወቀ፣ በህግ ለማስከበር የትኛውንም የአመራር አካልም ሆነ ጉባኤውን የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው። ብሎም በህግ ማስከበር ይችላል።

8. አንድ አባል ከደንቡ አግባብ ውጪ ከማህበሩ ያባረረውን አካል በህግ ከረታ ካሳ ይከፈለዋል፣ ተጠያቂነቱ ያባረረው አካል ይሆናል፣ ጉባኤው በወሰነው አካል ላይ ተመጣጣኝ ቅጣት ይወስዳል።

## አንቀጽ 30 የአባልነት ግዴታዎች:-

**1.** በስብሰባ ላይ መገኘት ።

**2.** የመተዳደርያ ደንቡን የማክበር ።

**3.** አመታዊ መዋጮን በደንቡ መሰረት የመፈፀም ።

**4.** የማህበሩን ንብረቶችን መገልገያዎች በአግባቡ የመጠቀም ።

**5.**የማህበሩ አባል የሆነ/ ች አባል ነፃ የኮሚኒቲ አገልግሎት መስጠት።

## አንቀጽ 31 ከአባልነት የሚያስወግድ ድርጊቶች:-

**1.** አንድ አባል ወይም አመራር በአንቀፅ **30** ላይ የተዘረዘሩትን የአባላነት ግዴታዎች ያለበቂ ምክንያት በአንድ አመት ክሰስት ወር ጊዜያቶች ማከናወን ካልቻሉ ከአባልነት ይወገዳሉ።

**2.** አንድ አባል ከአባልነት ከመወገዱ በፊት፣ በቅድሚያ ያጎደለውን እንዲያሟላ ሁለት ጊዜ ከስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ የፅሁፍ ማሳሰብያ ከጊዜ ገደብ ጋር ይላክለታል። በተሰጠው የግዜ ገደብ ካላሟላ ከአባልነት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት መሰረዙን የሚገልፅ ማስረጃ ከጠየቀ ይሰጠዋል።

**3.** አንድ አባል ከአባልነት ሲሰናበት የከፈለው ክፍያ አይመለስለትም።

**4.** ከአባልነት ከተሰረዘ በኋላ እንደገና በአዲስ ለመመዝገብ የመጨረሻ እድል ይሰጠዋል ።

**5.** አንድ አባል በሕዝብ ሆነ በውክልና ተመርጦ ሲያገለግል የያዘውን ስልጣንና የመገናኛ ብዙሃን ድምፅ በመጠቀም፣ የፖለቲካ ፣የሃይማኖት ፣የብሄር ተፅእኖ በሌሎች አባላት ላይ ካደረገና በማስረጃ ከተረጋገጠ ጉዳዩን ቦርድና ቁጥጥር ኮሚቴ በጋራ በማየት የመረጠው አካል በጉዳዩ ላይ እንዲወስን ያደርጋሉ። **Georgia code 14-**

**3-808 removal of directors(Board) elected by members or directors(Board).**

6. በማህበሩ ላልተመዘገቡና ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት በአባልነት ግዴታቸውን ለማይወጡ ማህበሩ አገልግሎት ለመስጠት ግዴታ አይኖርበትም።

## አንቀጽ 32 ምርጫ:-

## 32.1 የቦርድ አባላት አመራረጥ:-

**1.** የቦርድ፣ የስራ አስፈፃሚና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫ በየሁለት **(2)** አመቱ በታህሳስ (December) ወር የመጀመርያው ቅዳሜ ይከናወናል። ማንኛውም አዲስ አባል የሆነ ከስድስት**(6)** ወር በኋላ እኩል የመመረጥ መብት አለው።

2. የቦርድ አባላት፣ ከተለያዩ በ **501(C)(3) IRC** ስር ሆነው የተደራጁ ድርጅቶችና የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አባል ከሆኑ ሰዎች ብቻ የተመረጡ ተወካዮች በመላክ እና ከጠቅላላው ጉባኤ በቀጥታ ድምፅ ከተመረጡ ሰባት **(7)** የቦርድ አባላት ጋር በመሰብሰብ፣ በአስመራጭ ኮሚቴ አማካኝነት፣ ሊቀመንበር፣ም/ሊቀመንበርና፣ ጸሃፊ፣ በቦርድ ይሰየማሉ።

**3.** በማህበር የተደራጁ ተቋማት የቦርድ ተወካዮች መጠን :- ቁጥራቸው ከሃምሳ **(50)** በላይ የሆኑ የኮሚኒቲ አባላት ያላቸው ማንኛውም ተቋማት አንድነታችንን፤ ባህላችንን፤ ታሪካችንን ጠብቆ ለማቆየት ብቃታቸውና፣ ልምዳቸው ታይቶ አንድ**(1)** ወኪል በመላክ በምርጫው ቀን ከጠቅላል ጉባኤ ጋር የትውውቅ ስነ-ስርአት ይፈጽማሉ።

**4.** የቦርድ አባላት ቁጥር በጆርጅያ ህግ **14-3-803** መሰረት ተለዋዋጭ(variable) የሆነውን ደንብ በመጠቀም ከስምንት**(8)** እስከ አስራ ሰባት**(17)** ይደረሳል፣ ይህንን የቦርድ አባላት ቁጥር ለመቀየር የሚያጸድቀው ቦርዱ ለምልአተ ጉባኤው ባቀረበው ማሻሻያ ይወሰናል።

**5.** የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በዋነኛነት የተቋቋመበትና በ **IRS** ከግብር ነጻ የሆነው ባህሉንና ታሪኩን ለመጠበቅ በመሆኑ የቦርድ አደረጃጀትም ይህንን መሰረት ያደረገና ኢትዮጵያዊ አንድነትን የሚያስጠብቅ የምርጫ መስፈርት ነው። **501(C) (3) IRC.**

## 32.2 የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት አመራረጥ:-

**1.** ከምርጫው ቀን አንድ(1) ወር በፊት ከህዳር **1** እስከ **30** ቦርድ የአስመራጭ ኮሚቴ በማቋቋም፣ አስመራጭ ኮሚቴውም በመገናኛ ብዙሀንና በበራሪ ወረቀቶች የምርጫውን ቀን፣ ለውድድር የሚቀርቡ የስራ ክፍሎችን ዝርዝር ለአባላት ይፋ ይደርጋሉ። ( አስራ ሁለት**(12)** የስራ አስፈጻሚና ሶስት**(3)** ቁጥጥር ኮሚቴ)

**2.** የአስመራጭ ኮሚቴው፣ አንድነታችንን ፣ባህላችንና ታሪካችንን ጠብቆ ለማቆየት ብቃታቸውና ልምዳቸው ታይቶ ፍላጎት ያላቸውን አባሎች ጥቆማ ከአባላት ይቀበላል።

**3.** የአስመራጭ ኮሚቴው የተጠቋሚዎችን የሙያ ብቃትና ፍላጎት ካጣራ በኋላ የእጩዎችን ስም ዝርዝርና የሚወዳደሩትን የስራ ሃላፊነት ከሁለት ሳምት በፊት ለአባላት ይፋ ያደርጋል።

**4.** እጩ ተወዳዳሪዎች በመገናኛ ብዙሃን እራሳቸውን እንዲያስተዋውቁና ለወደፊት ኮሚኒቲውን ማሳደግ ብሎም በኢትዮጵያዊ አንድነት ዙርያ ላይ ለህዝብ ምኞታቸውን እንዲገልፁ ይመቻቻል

**5.**በምርጫው ቀን ጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ በመጥራት ምርጫው በግልፅ ይካሄዳል፣ አብላጫ ድምፅ ያገኙ እጩዎች አሸናፊ ይሆናሉ ውጤቱም በእለቱ ይገለጻል።

## አንቀጽ 33 የኮሙቴዎች የስራ ዘመን:-

**1.** በጉባኤና በውክልና ተመርጠው ሲያገለግሉ የነበሩትን በሙሉ የስራ ዘመን ሁለት**(2)** አመት ብቻ ነው።

**2.**በድጋሚ ለማገልገል የሚፈልጉ አመራሮች ፈቃደኛ ካሉና ወይም በድጋሚ ከተመረጡ፣ ለሁለተኛ ጊዜ በተከታታይ ለመወዳደር ይችላሉ።

**3.**ማንኛውንም የኮሚቴ አባል በተከታታይ ከሁለት **(2)** ግዜ በላይ ለምርጫ መወዳደርም ሆነ መወከል አይችሉም ለዚህ አፈፃፀም በወቅቱ ያለው አስተዳደር ተጠያቂ ይሆናል።

## አንቀጽ 34 የአስመራጭ ኮሚቴ

## ስልጣንና ተግባር:-

**1.** ቦርድ አምስት አባላት ያሉት ያስመራጭ ኮሚቴ ካዋቀሩ በኋላ የአስመራጭ ኮሚቴው ሊቀመንበርና ፀሃፊ ይመርጣሉ።

**2.** ምርጫን በተመለከተ ሙሉ ሃላፊነት በመውሰድ ገለልተኛ የሆነ ተጠያቂነት ያለው አሰራር ከማስመረጥ ጀምሮ ነባሩንና አዲሶቹን ተመራጮች ሃላፊነትን የማረካከብ ስራና የምርጫውን ሂደት በሰነድ በማስደገፍ ግልፅ የሆነ አሰራር ለመስራት ለኮሚኒቲው ጽ/ቤት አዲስ ለሚሾሙት ቦርድ ያስረክባሉ።

**3.** የምርጫውን አሰራር ይረዳል ባሉበትና ህዝብን ያሳትፋል በሚሉት ዘመናዊ በሆነ የጥቆማ መቀበያ ዘዴ በመጠቀም ከሃያ **(20)** ቀን ያላነሰ ግዜ በመስጠት ለአባላት እንዲደርስ ያደርጋሉ።

**4.** በየትኛውም ደረጃ በማህበሩ አመራርነት ላይ ያሉና ለወደፊቱም የሚመረጡ አዲስ እጩ ሃላፊዎች በድርጅት ውስጥ በክፍያ የሚሰሩና የንግድ ውል ያላቸው ባለቤትና ሰራተኛ እንዲሁም ቤተሰብ በአስመራጭ ኮሚቴነት እና በተመራጭነት አይሳተፉም። **IRS 501 (C) (3) public charities 4221-pc**

**5.** አስመራጭ ኮሚቴው የአሰራር ደንብን ለመከተል ጥቆማውና ምርጫው የሚያበቃበትን ግዜ ገደብ በይፋ በመገናኛ ብዙሃን ምርጫው ከመጀመሩ በፊት ማሳወቅ አለባቸው።

**6.** የአስመራጭ ኮሚቴ የስራ ዘመን በምርጫው ሂደትና ውጤት መሰረት ለጠቅላላ ጉባኤው የአዲሶቹ ተመራጮች የርክክብ ሂደት እስከሚያልቅ ድረስና የመጀመሪያ ስብሰባውን ሁሉንም በመጥራት የቦርድ አመራሮችን የሃላፊነት ምርጫ በማስመረጥና በመምራት የአመራሮች የሰነድና የስራ ልውውጥ በማድረግ የእንኳን ደስ አላችሁና የሽኝት ፕሮግራም በማዘጋጀት፣ የአስመራጭ ኮሚቴውም የመጨረሻው የስራ ጊዜ ቀን ይሆናል።

**7.** ምርጫው ከተጀመረ በኋላ ማራዘም አይቻለም በተውሰነለት ጊዜና ቀነ ማለቅ አለበት።

**8.** ምርጫው በአስመራጭ ኮሚቴ ከተጀመረ በኋላ ማንኛውም የማህበሩ አመራር የመደገፍ እንጂ ተፅእኖ የማድረግ ወይም አስመራጭን የመለወጥ ስልጣን የለውም ምርጫው ተጠናቆ በአዲስ አመራሮች እስኪተካ ድረስ የምርጫው ሃላፊነት የአስመራጮች ብቻ ይሆናል።

# አንቀጽ 35 ልዩ ድንጋጌ:-

የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በ**501(C) (3) IRC** ስር ከ **IRS** ከግብር ነጻ የሆነበት ዋንኛ መስፈርቱ ባህሉንና ታሪኩን ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ ነው።

**1.** የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አመታዊ በአል ታሪክንና ባህልን ለመላው አለም ህዝብ የሚያስተዋውቅበት፣ አመታዊ ባጀቱን የሚሸፍንበት፣ የኢትዮጵያ ባንዲራ በአትላንታ ከተማ ከፍ ብሎ የሚውለበለበት ልዩ ቀን ነው፣ በኢትዮጵያ ጥላ ስር አንድ ሆነን የምንሰባሰበት፣ የኢትዮጵያውያን አዲስ አመት ተብሎ ይጠራል።

**2.** ለሀገራችን የሰላም የብልፅግና ያድርግልን የምንልበት በመሆኑ በየትኛውም አመራር ላይ ያለ ሃላፊነት ወስዶ የሚከበርበትና ጊዜና ወቅቱን የጠበቀ በአል እንዲሆን በኢትዮጵያውያን ቀን አቆጣጠር ከመስከረም ሃያ **(20)** ቀን ማለፍ የለበትም። ምንም አይነት ምክንያት አመታዊ በአሉን የሚያስቀር ወይም የሚያስተላልፍ ጉዳይ ሊኖር አይችልም፣ የኮሚኒቲውም በጀት በመሆኑ በህግ ያስጠይቃል።

**3.** የምርጫ ጊዜ ወሰን በወቅቱ ያሉት አመራሮችን የሚያስጠይቅና ሃላፊነትን ከመወጣት አኳያ በደንቡ ላይ ከተቀመጠበት ቀን ጀምሮ ከሁለት **(2)** ወር ከአስራ አምስት**(15)** ቀን በላይ ማለፍ የለበትም ያስጠይቃል፣ የአንድ አባል የመጨረሻውና ትልቁ መብት ምርጫ በመሆኑ ምንም አይነት ጉዳዮች ምርጫን ሊያስተጓጉሉ ወይም ሊያስቀይሩ አይችሉም። [አንቀጽ **33** ቁጥር **1** የሁለት አመት ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ]።

**4.** የመተዳደሪያ ደንቡን የሚያፀድቀው ሙሉ ስልጣን የምልአተ ጉባኤው ብቻ ነው።

**5.** የአድዋ ድል ፣ የየካቲት **12** የሰማዕታትና የካራ ማራ የድል በአል ኢትዮጵያ ኮሚኒቲ የሚያከብረው:- ለመላው አለም ጥቁር ህዝቦች የነፃነት ምልክት በመሆኑም ጭምር ነው። ባህልን ታሪክን፣እምነትን መጠበቅና ለትውልድ የማስተላለፍ ዋንኛ የኮሚኒቲው መሰረቱም ይህንን የብዙ- ሺህ አመት ታሪክና አንድነትን፣ ቀና ብሎ የሚኖር ህዝብ መሆኑን ለልጆቻችን የምናስተላልፍበት የድል በአል ነው።

**6**. የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ:-ምንም አይነት ምልክት የሌለብት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ፣ ነው። በኮሚኒቲው ቢሮ ፊት ለፊት ምን ግዜም ከአሜሪካ ባንዲራ ጋር ጎን ለጎን በሚታይ ቦታ ከፍ ብለው ይውለበለባሉ።

**7.**ባንዲራው ዝቅ ብሎ የሚውለበለበው በምንኖርበት ሀገር አሜሪካ ህግ መሰረት ለሃዘን ጊዜ ብቻ ነው።

**8.** በምንኖርበት አሜሪካ ህግ አንድ ድርጅት ወይም ሰው የመክሰስና የመከሰስ መብት እንዳለው ሁሉ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲም ለመክሰስ የድርጅቱን በጀት የሚጠይቅ በመሆኑ ሁሉም ኮሚቴ ቦርድ፣ የስራ አስፈፃሚ፣ ቁጥጥር ኮሚቴ በመሰብሰብ **3/4** በሆነ ድምፅ አውንታዊ ማግኘትና በቃለ ጉባኤ የተፈራረሙበትን ለጉባኤው ማቅረብ አለባቸው።

**9.** ውል ወይም ኮንትራት በተመለከተ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አመራሮች ከአንድ(1) አመት ያልበለጠና በእያመቱ የሚታደስ ወይም የሚሻሻል ኮንትራት መዋዋል ይችላሉ፣ የአመራር ምርጫ በሚደረግበት በሶስት**(3)** ወር ጊዜ ውስጥ ውሎችን ወይም ኮንትራት መዋዋል አይችሉም ሆኖም ግን ለቀጣዩ አዲስ አመራሮች ሰነዶችን ማመቻቸት ይችላሉ።

**10**. በስራ አስፈጻሚ የሚሰሩ ማንኛዉም የስራ ቅጠራና ከግለሰብ ወይም ድርጅቶች ጋር የሚኖር ኮንትራቶች ወይም ውል ከመደረጉ በፊት ከኮሚኒቲው ቦርድ ፈቃድና የውሳኔ ቃል ጉባኤ የተያዘ መሆኑን መረጋገጥ እለብት።

**11.** የቋንቋ ቅደም ተከተል በህግ ትርጓሜ:- የእነዚህ መተዳደሪያ ደንቦች ሁለት ቅጂዎች አሉት (አማርኛ እና እንግሊዘኛ) ሁለቱም ቅጂዎች ትክክለኛ እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ፣ ለህጋዊ አሰራር የአማርኛ ቅጂ ለትርጉም ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።

**አንቀጽ 36 መተዳደሪያ ደንቡ የሚፀናበት ግዜ:-** ይህ መተዳደሪያ ደንብ ከ____ ___ቀን___( ) ጀምሮ በስራ ላይ ይውላል። ከዚህ በፊት የነበሩ የመተዳደርያ ደንቦች ይህ ደንብ በስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ተሽሯል።

## አንቀጽ 37 መተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻልበት ሁኔታ:-

**Georgia codes 14-3-1021 AMENDMENT WHERE VOTE OF MEMBERS REQUIRED.**

**1.** ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል ።

**2.** ከቦርድ አባላት **2/3** ድምፅ ወይም 1/3 የማህበሩ አባላት ከጠየቁ ቦርድ በማሻሻል ለምልአተ ጉባኤው አቅርቦ ሊሻሻልና ሊያፀድቀው ይችላል።

**3.** ይህ ደንብ እንዲሻሻልና እንዲጸድቅ የመጨረሻውን ውሳኔ የሚወስነውና ለቀረበው ማሻሻያ የሚያፀድቀው በጆርጅያ ህግ መሰረት **1/10** የተሰበሰበው አባላት ብዛት ተገኝቶ **2/3** ድምፅ የሆነው ምልአተ ጉባኤው ሲስማማበት ብቻ ነው ( አንቀጽ አስር **(10)** ቁጥር ዘጠኝ ( **9** ) እንደተጠበቀ ሆኖ )። **Georgia code 14-3-722**

## የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር በአትላንታ፤
## የፈጠረን አምላክ ሀገራችን ኢትዮጵያንና አሜሪካን ይባርክ፣
## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።